በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ህዳር 20 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# 76ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 76ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በኢንቨስትመንት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ አምራች እና አስቻይ ኢንቨስትመንት መስኮችን ጨምሮ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ በማበረታታት እና በማስፋፋት አገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን፣ የዕድገቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ማጠናከር እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እንዲሁም የአገራዊ ኢኮኖሚውን አለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነት የሚያፋጥን፣ የወጪ ንግድን የሚያስፋፋ፣ ሰፊ እና ጥራት ያለው የስራ እድል የሚፈጥር፣ በተጨማሪም በተለያዩ ዘርፎች መካከል ዘላቂ እና ተመጋጋቢ ትስስርን የሚያሳልጥ የኢኮኖሚ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በቀረበ የፕራይቬታይዜሽን ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ እና ለግል ኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ የፖሊሲ ከባቢዎችን ለመፍጠር፤ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ አፈጻጸም አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ ለልማት የሚውልን የፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑና የግል ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ሚናና ተሳትፎ ማስፋፋትና ማዳበር ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ቅልጥፍና ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ ለካፒታል ያላቸውን ተደራሽነት እና የአገልግሎታቸውን ጥራትና ተደራሽነት ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ የገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር ረቂቅ (የፕራይቬታይዜሽን ረቂቅ አዋጅ) አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. ሌላው ምክር ቤቱ የተመለከተው የኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ ነው፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ በታክስ አሰባሰብ ረገድ ቅልጥፍናን እና ቁጥጥርን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በማስጠበቅ የኤክሳይዝ ታክስ ከተጣለባቸው ምርቶች መንግስት ተገቢውን ታክስ መሰብሰብ እንዲችል የሚያግዝ፣ ኮንትሮባንድ እና ህገ ወጥ ንግድን በመከላከል ረገድ አስተዋጽኦ የሚያደርግ እንዲሁም የህብረተሰቡን ጤና በሚጎዱና የማህበራዊ ችግር በሚያስከትሉ በተጨማሪም መሰረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ተፈላጊነታቸው በማይቀንስ እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ታክስ መጣል በማስፈለጉ የገንዘብ ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ማሻሻያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ም/ቤቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ ዘመናዊና ተደራሽ በማድረግ ሀገሪቱን ለንግድ ስራ መጀመር ምቹ እንድትሆን ለማስቻል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ስርአትን የሚያስተዳድሩ ህጎች ላይ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009 ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

//